# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 57 ሰኔ 11 2001 ዓ.ም


“ኤፈርት /በትግርኛው ምህፃር ‹‹ትእምት››/ ወያኔ በረሃ እያለ ባንኮችን፣ የመንግሥት መኪናዎችን እና የግለሰቦችን ንብረት በመዝረፍ ያቋቋመው ህገ-ወጥ የዘራፊዎች ድርጅት ነው”

**ርዕሰ አንቅጽ**

## ወያኔ በእነ ጄ/ል ተፈራ ማሞና በሌሎችም እስረኞች ላይ አሰቃቂ ድርጊቶችን እየፈጸመ ነው

ወያኔ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሊያደርጉብኝ ሲሉ ያዝኩዋቸው በሚል የሀሰት ውንጀላ ዘብጥያ ባወረዳቸው በእነ ጄ/ል ተፈራ ማሞና በሌሎችም እስረኞች ላይ አሰቃቂ ድርጊቶችን እየፈጸመ እንደሚገኝ የእስረኞች ቤተሰቦች አጋለጡ።

ለመውደቅ ትንሽ የቀረው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከግንቦት 7 ጋር አያይዞ በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ባሰራቸው የመከላከያ ሰራዊት አባላትና ሲቪሎች ላይ እጅግ ጭካኔ የተሞላው ድረጊት እየፈጸመባቸው እንደሆነ ረዩተር የእስረኞችን ቤተሰቦች ዋቢ አድርጎ ዘግቧል።

ተስፋ እየቆረጠ የመጣው የወያኔ አገዛዝ፣ በእስረኞች ላይ ግፍ እየፈጸመ እንደነበር የግንቦት 7 ድምጽ ቀደም ብሎ መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን፣ በረዩተር ይፋ የሆነው መረጃ እንደሚያመለክተው ደግሞ በእስረኞች ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ በዚህ ዘመን ይፈጸማል ተብሎ የማይታሰብ ነው። ከታሳሪዎች መካከል ብልታቸውን የተቀጠቀጡ፣ አጥንታቸውን የተሰበሩ፣ በኤሌክትሪክ ሽቦ የተገረፉ፣ የውስጥ እግራቸው ተገልብጦ የተገረፉ መኖራቸውን ከውስጥ ምንጮች ያገኘነው መረጃ ያመልከታል። እስረኞቹ አሰቃቂ ድብደባ ከተፈጸመባቸው በሁዋላም “ምንም የምናውቀው ነገር የለም የሚል መልስ” ከመስጠት በስተቀር ፣ ወያኔን ሊጠቅም የሚችል ምንም አይነት መረጃ አለመስጠታቸውም ታውቋል። በእስረኞቹ ጽናት የተበሳጨት ወያኔዎች ተጨማሪ የማሰቃያ ዘዴዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ትእዛዝ ማስተላለፋቸወም ታውቋል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## በወያነ መንደር ትርምሱ ቀጥሏል

የፍትህ ሚኒስትር የነበሩትና የፕሬዚዳንቱ ፅህፈት ቤት ተሿሚ የሆኑት አሰፋ ከሲቶ- በፖሊሶች እየተዋከቡ ቤታቸውን ለቀቁ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የፍትህ ሚኒስትር የነበሩትና በአሁኑ ወቅት የፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ አማካሪ ተብለው ያለፋይዳ የተቀመጡት አቶ አሰፋ ከሲቶ፤ከበላይ አካል በተላለፈ ትዕዛዝ ቀደም ሲል ተሰጥቷቸው ከነበረው ቤት በፖሊስ እየተዋከቡ እንዲለቅቁ መደረጋቸው ታወቀ።

የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ያጠናቀረው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ፤በተለይ የግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ በመገናኛ ብዙሀን ያለማሳለስ ስማቸው ሲናኝ የነበሩት አሰፋ ከሲቶ ፤ከወያኔ የተሰጣቸውን የአገልግሎት ተልዕኮ በማጠናቀቃቸው ፤በሌሎች እንደተደረገው ሁሉ- የፍትህ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ ተሰጥቷቸው ከነበረውና በብስራተ-ገብርኤል አካባቢ ከሚገኘው ቤታቸው ባለፈው ሰኞ በፖሊስ ተገደው ከነእቃቸው ሜዳ ላይ ተጥለዋል።

አሰፋ ከሲቶ በሚያሳዝንና ውርደት በተሞላበት ሁኔታ በፖሊስ እየተዋከቡ እንዲወጡ የተደረገው ሆነ ተብሎ በጋዜጠኞች ፊት ነው ያለው ዘጋቢያችን፤ፖሊሶቹ ከቤት የማስወጣቱንና የማዋከቡን ተግባር ይፈፅሙ የነበረው በስልክ እየተደዋወሉና ትዕዛዝ እየተቀበሉ እንደነበር መመልከቱን ገልፁዋል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ከ9 ሚልዮን በላይ ህዝባችን በከፍተና የርሃብ አደጋ ላይ ነው

የልማት መንግሥት ነኝ ባዩ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በሚያስተዳድረው አገራችን አሁንም ረሃብ ከፍተኛ አደጋ መሆኑ ተዘገበ:: ከ9 ሚልዮን በላይ ህዝባችን በከፍተና አደጋ ላይ ነው ተባለ:: ለአለፉት18 አመታት በስልጣን ላይ ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ፣ አገሪቱን ለአስከፊ ረሀብ መዳረጉን በኢትዮጵያ የሚሰሩ አለማቀፍ ድርጅቶች አጋለጡ።

በዘ ወርልድ ቱዳይና በቢቢሲ ድህረገጾች ላይ የወጡት ዜናዎች እንደሚያመለክቱት በአገሪቱ የታየው የርሀብ አደጋ ከምንግዜውም በእጅጉ የከፋ ነው። የዘረኛው መለስ ዜናዊ መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ ህዝቡን በቀን ሶስት ጊዜ እንዲበላ አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን በማስታወስ አስተያየት የሰጡን አቶ ተስፋየ አሰግድ የተባሉ የዲሲ ነዋሪ እንደተናገሩት፣ መለስ ዜናዊ ከ18 አመታት የስልጣን ጊዜ በሁዋላ ህዝቡን እንኳን በቀን ሶስት ጊዜ ሊያበላው ቀርቶ አንድ ጊዜም አብልቶ ለማሳደር እንዳልቻለ ተናግረዋል። ጥቂት ለአገዛዙ ያደሩ ሰዎች የቅንጦት ኑሮ እየኖሩ ቢሆንም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግን የሚበላው አጥቶ በመሰቃየት ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የወያኔ ሁለገብ ዘረፋ መጋለጡን ቀጠለ ። ስዩም መስፍን በሚስት ስም ከሙገር ስምንቶ ፋብሪካ ሃብት እያካበተ ነው

የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ የቦርድ ሊቀመንበር የሆነው ስዩም መስፍን ሚስቱን የሲሚንቶ አከፋፋይ አድርጎ ከፍተኛ ገንዘብ እየመዘበረ እንደሆነ የግንቦት ሰባት የአዲስ አበባ ዘጋቢ የላከልን ሪፓርት አመለከተ። የውስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሶ ዘጋቢያችን ያደረሰን ዜና ሳባ የተባለችው የስዩም መስፍን ሁለተኛ ሚስት በአዲስ አበባ ትልቅ የኮንትስትራክሽን ኩባንያ በባለቤትነት እንደምትመራ እና የሙገር ሲሚንቶን አየር በአየር እንደምትቸበችብ አመልክቷል።

አንድ ኩንታል ሲሚንቶ በአንድ መቶ ስልሳ ብር ገዝታ ለተጠቃሚዎች ከሶስት መቶ ሰማንያ እስከ አራት መቶ ብር ድረስ የምትቸበችበው የስዮም መስፍን ሚስት ከሲሚንቶ ብቻ በርካታ ሚሊዮን ብር ማግበስበሷን ምንጮቹ አጋልጠዋል። የወያኔ አባል ያልሆነ ወይም ከወያኔ ጋር ያልተዛመደ ኮንትራክተር እና ቤት የሚያሰራ ግለሰብ የሙገር ሲሚንቶን ለማግኘት ፈታኝ የሆነ ደጅ ጥናት እንዳለበት እና የሚፈልገውን ማግኘት ህልም እንደሆነበት ተዘግቧል።

ቱባ ቱባ የወያኔ ባለስልጣኖች እና የጦር አለቆች በሚስቶቻቸው እና በዘመዶቻቸው የሀገርን እና የወገንን ንብረት ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ እያጋጡ እንደሚገኙ ከማንም ኢትዮድያ የተደበቀ አይደለም።ወያኔዎች በግለሰብ ደረጃ ከሚፈጽሙት የቀን ተቀን ዝርፊያ በተጨማሪ ፋብሪካ አቋቁመው ተሰምቶ በማይታወቅ መንገድ የህዙቡን ማጅራት መምታታቸው ግልጽ ነው። በገበያ ላይ ተፈላጊነት ያለውን ሙገር ሲሚንቶን በራሳቸው ከተቆጣጠሩት በኋላ እና በሚፈልጉት መንገድ ከቸበቸቡት በኋላ ከኤፈርት ድርጅቶች አንዱ የሆነው መሶበ ሲሚንቶ ፋብሪካ የሚያመርተውን ጥራቱን ያልጠበቀ ሲሚንቶ ተጠቃሚው በግድ እንዲገዛ ጫና እንደሚያደርጉ ታውቋል። ከዚህም በተጨማሪ ትግራይ ላይ የተመረተን ሲሚንቶ በሙገር ስሚንቶ ማሸጊያ እንዲታሸግ ተደርጎ የሙገር ምርት ከሚሸጥበት ዋጋ በአራት ብር ቅናሽ እየተሸጠ እንደሆነ ዘጋቢያችን የውስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሶ ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል ።

በወያኔ የሚፈጸመው ሀገራዊ ዝርፊያ እና ቅሚያ የሀገሪቱን ካዝና ማራቆቱን እና ህዝቡን በገዛ ሀገሩ ላይ የበይ ተመልካች ካደረገው መሰንበቱ ይታወቃል። እንደ አዜብ መስፍን እና ሳባ አይነት የድህን ህዝብ ገንዘብ በልተው የማይጠረቁ የቀን ጅቦች በከተማው እና በሀገሩ ነግሰው ባለበት ሁኔታ ለፍትህ እና ለርትእ መቆም እንደሀጢያት ተቆጥሮ እነ ብርቱኳንን የመሳሳሉ ብርቅ የኢትዮድያ ልጆች ፍጹም አረመኔያዊ እና ፋሺስታዊ በሆነ ጭካኔ ሲሰቃዩ ማየት ለህሊና ጸጸት ይዳርጋል ተብሎአል። በጉዳዩ ላይ ያነጋገርናቸው አንድ ታዛቢ ረሀብ አጥንቱን ባገጠጠው ህጻን፤ ችጋር ልጡን ባራሰው አረጋዊ ስም ተለምኖን የሚመጣ ገንዘብ የሚዘርፉ፤ ታታሪውን ነጋዴ በተቆጣጠሩት መንግስታዊ ስልጣን በመጠቀም በጠረባ እየመቱ በአቋራጭ የከበሩት ወያኔዎች ተንደላቀው ሙቅ ሲያኙኩ፤ ሲያስሩ እና ሲገድሉ ዝም ማለት ከእነሱ ጋር በሀገራዊዊ ወንጀል ከመተባበር ይቆጠራል ብለዋል።

በዚህ አስቀድሞ በተጠና እስትራጂ ምክንያት ነዉ ወያኔ ፓለቲካውን እንደተቆጣጠረ ወዲያውኑ እጆቹን ወደ ኢኮኖሚው ያዞረው፡፡ በኢኮኖሚ የበላይነት ካልተገደፈ የፓለቲካ የበላይነት ዘላቂነት አይኖረውም የሚል እሳቤ ከሌኒን ተምረው መምህራቸውን በልጠዋል፡፡ እንደሚታወቀው ባሁኑ ሰዓት በጣም ከሚወራለት ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጀምሮ እስከ ጉሊት ችርቻሮ ወያኔ ያልገባበት ንግድ የለም፡፡

ከኢኮኖሚው ቀጥሎ የተዘመተባቸዉ ደግሞ የሲቪል ማኅበራት ናቸው፡፡ የሲቪል ማኅበራትን የመጠቅለል አስፈላጊነት ለመገንዘብ በነሌሊን አስተምህሮት መቆም አይበቃም፡፡ ተግባራዊ ልምድን ከስታሊንና ፣ ኤንቨር ሆዣ መውሰድ ይፈልጋል፡፡ ወያኔ እንደዚህ ተጨንቆ ያጠናውን ነው ዛሬ እየተገበረው ያለው፡፡

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

“አስቀድሞ በተጠና እስትራጂ ምክንያት ነዉ ወያኔ ፓለቲካውን እንደተቆጣጠረ ወዲያውኑ እጆቹን ወደ ኢኮኖሚው ያዞረው፡፡ በኢኮኖሚ የበላይነት ካልተገደፈ የፓለቲካ የበላይነት ዘላቂነት አይኖረውም የሚል እሳቤ ከሌኒን ተምረው መምህራቸውን በልጠዋል፡፡ ....ከኢኮኖሚው ቀጥሎ የተዘመተባቸዉ ደግሞ የሲቪል ማኅበራት .....የሃይማኖት ተቋማት... ...የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት .. የሙያ ማኅበራት ቀጥሎ ግብረሰናይ ድርጅቶች በህግ ሰንሰለት ታሰሩ፤ እያለ .. እያለ .. ወረደና ባሁኑ ሰዓት የስፓርት ቡድኖች፣ ሰንበቴዎች፣ እድሮችና እቁቦች ሳይቀሩ በወያኔ ቁጥጥር ሥር የማድረግ ሥራ ተያይዞታል፡፡ በዚህ ከቀጠለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቡና ተርቲቦችም የወያኔ መፈንጫ ይሆናሉ” **ዶ/ር ታደሰ ብሩ**

### «ኤፈርት መር ካፒታሊዝም» የዘራፊዎች ካፒታሊዝም በመሆኑ አጥብቅን እንዋጋዋለን፡፡

የወያኔ የተውገረገረ የኢኮኖሚ ፓሊሲ ምንነት እንደሰሞኑ የስብሃት ነጋ ቃለ-መጠይቅ ይፋ ያወጣ የለም፡፡ ስብሃት የድርጅታቸው የኢኮኖሚ ፓሊሲ ግብ ካፒታሊዝም መሆኑን ነገረን፡፡ ይህ አባባሉ የአፍ ወለምታ ሳይሆን ተዘጋጅቶ እንደመጣበት «ካፒታሊዝም» የሚለውን ቃል ከሚገባው በላይ በመደጋገም አረጋገጠልን፡፡ ኤፈርት ለካፒታሊዝም በኢትዮጵያ እውን መሆን እንደሚተጋም ተከራከረ፡፡ ቀጥሎም የካፒታሊስቱ መደብ ሲጎለብት ኢህአዴግ ስልጣኑን አስረክቦ እንደሚከስም ቃል ገባ፡፡

በወያኔዎች «አቦይ» እየተባለ የሚቆላመጠው ስብሃት ነጋ ከዚህም በላይ ብዙ የዘባረቀ ቢሆንም ለጊዜው በእነዚህ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡

ለመሆኑ ስብሃት ነጋ በግል፤ ወያኔ እንደ ቡድን ካፒታሊዝምን ያውቁታል? ስለ ካፒታሊዝም ብዙ እጅግ ብዙ የተባለና ወደፊትም ብዙ የሚባል ቢሆንም ቢያንስ የሚከተሉት ሶስት ነጥቦች መሠረታዊ ናቸው፡፡

1. ካፒታሊዝም በግለሰብ ነፃነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ነው፡፡ ለዚህም ነው ካፒታሊዝምና ዲሞክራሲን ነጣጥሎ ማየት አስቸጋሪም አሳሳችም ነው የሚባለው፡፡
2. የካፒታሊዝም መሠረቱ የግል ሃብት ነው፡፡ በካፒታሊዝም መንግሥት በኢኮኖሚ ላይ ያለው ተሳትፎ ፍትሃዊ ፓሊሲዎችን በማውጣትና በማስፈፀም ላይ የተወሰነ ሲሆን፤ መንግሥት በገበያ ውስጥ ጣልቃ የሚገባው ከግሉ ኢኮኖሚ በተሻለ ይሰራቸዋል በሚባሉ ተግባራትና ጊዜዓት ብቻ ነው፡፡
3. በካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሥልጣን እና የፓለቲካ ሥልጣን የተለያዩ ናቸው፡፡ ሃያማኖትና መንግሥት እንደተለያዩ ሁሉ ገንዘብና የመንግሥት ሥልጣንም የተለያዩ ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ሶስት መሠረታዊ ነገሮች ያልያዘ ሥርዓት ካፒታሊስታዊ ነው ሊባል አይችልም፡፡

የወያኔ ካፒታሊዝም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ለአንዳቸውም ደንታ የለውም፡፡ በወያኔ ሊገነባ የታቀደው ካፒታሊዝም ነፃነትን ሳይሆን ባርነትና ዘረፋን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እንደ ስብሃት አነጋገር በወያኔዎች ጭንቅላት ውስጥ ያለው ካፒታሊዝም ሳይሆን ኢምፔሪያሊዝምን ይመስላል፡፡ «ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም» ብዙዎችን እያደኸየ ጥቂት የወያኔ ጎጠኞ ገገዎችን ግን በሃብት እያንበሻበሸ መሆኑ እና ወያኔ ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው በወረራ እንደያዛት አገር የመሆኑ እውነታ እየገነቡት ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓትን እነሱ «ካፒታሊዝም» ብለው ቢጠሩትም ከካፒታሊዝም ይልቅ ለኢምፔሪያሊዝም ይቀርባል፡፡ «ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ነው» የሚለው ሌሊናዊ ቀኖና ለወቅቱ ሁኔታ ሲያስማሙት «ካፒታሊዝም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ከፍተኛውና የመጨረሻ ደረጃ ነው» ወደሚል አስቂኝ መደምደሚያ እንደደረሱ ልብ ይሏል፡፡

ለወያኔዎች ካፒታሊዝም ማለት ጥቂት ሃብታሞች ያሉበት ሥርዓት ማለት ሲሆን፤ የሚሊኒየሮች መኖር ደግሞ ለካፒታሊዝም መገንባት ማረጋገጫ ነው፡፡ ስብሃት አይናገረው እንጂ የጦር መኮንኖቻቸውና ባለሥልጣኖቻቸው በጥቂት ዓመታት ውስጥ ባለብዙ ሚሊዮኖች መሆን የካፒታሊዝም ውጤት አድርገው ይወስዱታል፡፡ ወያኔ የዛሬ ዓመት ግድም ሚሊየነር ስለሆኑ ገበሬዎች መፈጠር ነግሮን ነበር፤ አሁን ያ ወሬ ሲነፍስበት በኤፈርት ተኩልን፡፡

ለመሆኑ ኤፈርት ምንድነው? የማነው? የ ስብሃትን ማጭበርበሪያ ወዲያ ጥለን ኤፈርት ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ምን ማለት እንደሆነ ባጭሩ እንግለጽ፡፡

ኤፈርት /በትግርኛው ምህፃር «ትእምት»/ ወያኔ በረሃ እያለ ባንኮችን፣ የመንግሥት መኪናዎችን እና የግለሰቦችን ንብረት በመዝረፍ ያቋቋመው ህገ-ወጥ የዘራፊዎች ድርጅት ነው፡፡

ወያኔ የሚኒሊክ ቤተመንግስትን ከተቆጣጠረ ወዲህም ኤፈርት ራሱን በአስራ ሶስት ግዙፍ ኩባንያዎች አደራጅቶ በሁሉም አቅጣጫ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በመቦጥቦጥ የወያኔ ሹማምንትን ኪስ እንዲያደልብ አደራ ተጥሎበታል፡፡ በዚህም መሠረት *መሰቦ የኮንስትራክሽን ግብዓት ማምረቻ፣ መሰፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ፣ አዲስ የመድሃኒት ማምረቻ፣ ኢዛና የማዕድን ልማት፣ ጉና የንግድ ድርጅት፣ ሕይወት የግብርና ሜካናይዜሽን፣ ሳባ እብነ በረድ ማምረቻ፣ ሼባ የቆርቆሮ ፋብሪካ፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ አልሜዳ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ኤክስፐረስ የትራንዚት አገልግሎት፣ ኢትዮጵያን እንወቅ አስጎብኚ ድርጅት እና ትራንስ ኢትዮጵያ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት* የተሰኙ ግዛዙፍ ኩባንያዎችን አቋቁሞ ስብሃት እንዳለውም በመላው ኢትዮጵያ ተንሰራፍቷል፡፡

ይህም አልበቃ ብሎ በቅርቡ ደግሞ *ብሩህ ተስፋ ፕላስቲክ ፋብሪካ፣ ማይጨው ፓርቲክል ቦርድ ፋብሪካ፣ ዲማ የማር ማጣሪያ፣ አላጌ ደንና የደን ውጤቶች፣ ናሽናል ጂኦ-ቴክስታይል እና አበርደሌ የእንስሳት ማድለቢያና ኢክስፖርት ድርጅት* የተባሉ ስድስት ኩባንያዎች የያዘው ደጀና ኢንዳውመንት ተጨምሮለት የበለጠ እንዲንሰራፋ ከተደረገ በኋላ አዜብ መስፍን በቅርበት እንድትቆጣጠረው በምክትል ሥራ አስኪያጅነት ተመድባለች፡፡

ከላይ የተዘረዘረው ኤፈርት በአደባባይ የሚሰራውን ነው፡፡ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በቅርበት የሚከታተሉ እንደሚያውቁት ሁሉ ኤፈርት በኮንትሮባንድ ንግድ ጭምር የገባ ከመሆኑም በላይ ያሻውን ያህል ተበድሮ ያለመክፈል ልዩ ፈቃድ ያለው ቅምጥል ድርጅት ነው፡፡ ለማስረጃም ያህል ብዙ ድርጅቶች በባንክ እዳ በሃራጅ ሲሸጡ ለኤፈርት ግን ከሶስት ቢሊዮን በላይ የባንክ እዳ ተዘርዞለታል፡፡ እንዲያም ሆኖ ኤፈርት የጌቶቹን ኪስ በመሙላት እንጂ በአትራፊነቱ እጅግም የሚታወቅ ድርጅት አይደለም፡፡ ባጭሩ ኤፈርት ኢትዮጵያን በመዝረፍ ተቋቁሞ አሁንም በመዝረፍ ላይ ያለ የወያኔዎች የማይሞላ ቀዳዳ ኮሮጆ ነው፡፡

የወያኔ የኢኮኖሚ ፓሊሲ ቀድሞ ይታወቅበት ከነበረው «ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት» ወደ «ኤፈርት መር ካፒታሊዝም» መሸጋገሩን አቦይ ስብሃት ሲገልፅልን የሚያልሙት ካፒታሊዝም «የዘራፊዎች ካፒታሊዝም» ስለመሆኑ ከራሱ ከኤፈርት ሌላ ዋቢ አያሻም፡፡

በኤፈርትም ሆነ ሌሎች መሰል ኩባንያዎች ሽፋን እየተደረገ ያለው ዘረፋ ማስቆም የዚህ ትውልድ ግዴታ ነው፡፡ ኤፈርት መር ካፒታሊዝም የሽፍቶች ካፒታሊዝም በመሆኑ ማንኛውም ቅን ዜጋ አጥብቆ ሊዋጋው ይገባል እንላለን ::




የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 57 ሰኔ 11 2001 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# ለነፃነት በምናደርገው ትግል የሲቪል ማኅበራት ሚና

በለንደን ስብሰባ የቀረበ ታደሰ ብሩ (ዶ/ር)

## መግቢያ

ፍፁም የሆነ አምባገነን ሥርዓት ለማስፈን ፓለቲካውን ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚውንም ሲቪል ማኅበራትንም የመቆጣጠር አስፈላጊነት የነመለስ የተጠና የስትራቴጂ አቅጣጫ ይመስለኛል።

በኔ ግምት በዚህ አስቀድሞ በተጠና እስትራጂ ምክንያት ነዉ ወያኔ ፓለቲካውን እንደተቆጣጠረ ወዲያውኑ እጆቹን ወደ ኢኮኖሚው ያዞረው። በኢኮኖሚ የበላይነት ካልተገደፈ የፓለቲካ የበላይነት ዘላቂነት አይኖረውም የሚል እሳቤ ከሌኒን ተምረው መምህራቸውን በልጠዋል። እንደሚታወቀው ባሁኑ ሰዓት በጣም ከሚወራለት ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጀምሮ እስከ ጉሊት ችርቻሮ ወያኔ ያልገባበት ንግድ የለም።

ከኢኮኖሚው ቀጥሎ የተዘመተባቸዉ ደግሞ የሲቪል ማኅበራት ናቸው። የሲቪል ማኅበራትን የመጠቅለል አስፈላጊነት ለመገንዘብ በነሌኒን አስተምህሮት መቆም አይበቃም። ተግባራዊ ልምድን ከስታሊንና ፤ ኤንቨር ሆዣ መውሰድ ይፈልጋል። ወያኔ እንደዚህ ተጨንቆ ያጠናውን ነው ዛሬ እየተገበረው ያለው።

የሃይማኖት ተቋማት የመጀሪያዎቹ የጥቃት ሰለባ ሆኑ፤ በማከታተልም የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት ተያዙ፤ ከዚያም የሙያ ማኅበራት ተጠለፉ፤ ቀጥሎ ግብረሰናይ ድርጅቶች በህግ ሰንሰለት ታሰሩ፤ እያለ .. እያለ .. ወረደና ባሁኑ ሰዓት የስፓርት ቡድኖች፣ ሰንበቴዎች፣ እድሮችና እቁቦች ሳይቀሩ በወያኔ ቁጥጥር ሥር የማድረግ ሥራ ተያይዞታል። በዚህ ከቀጠለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቡና ተርቲቦችም የወያኔ መፈንጫ ይሆናሉ።

ንግግሬ የአካዳሚክ ዲስኩር እንዳይመስልብኝና አድማጮቼን እንዳላሰለች እየተጠነቀቅሁ ስለሲቪል ማኅበራት ምንነት፣ ወያኔ ለምን ሊቆጣጠራቸው አጥብቆ እንደፈለገ፤ የወያኔ ቁጥጥር በአገራችን፣ በህዝባችንና በራሳችን ሕይወት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት እና ይህ እንዳይመጣ ማድረግ ስላለብን ነገሮች አንዳንድ ጥቅል ሃሳቦችን ለወደፊት ውይይት በመነሻ ሃሳብነት አቀርባለሁ።

## ትርጓሜ

ሰዎች ለብቻቸዉ ሊከውኗቸው የማይችሏቸው ተግባራት በርካታ ናቸው። በስልክ እንኳን ለመደሰት ቢያንስ የአንድ ሰው ትብብር ይፈልጋል - እንዲደውል ወይም እንዲደወልለት። የብቻ የእግር ኳስ ጨዋታም አይጥምም። በጋራ የሚሠራ ነገር ሁሉ ሰዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ማደራጀት ይፈልጋል። ይህ ደግሞ በተራው የጋራ ግዛቤን፣ የጋራ ፍላጎት እና መተማመንን ይፈልጋል። ስለሆነም ለሐዘንም ይሁን ለደስታ፣ ወይም ሙያን ለማዳበር፣ ወይም አብሮ ለመጸለይ ወይም ደግሞ ቡና ለመጠጣጣት ስንል አውቀንም ሆነ ሳናውቅ ማኅበራትን እንፈጥራለን። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ከቤተሰብ ድንበር የዘለሉ፣ ከመንግሥት ቀጥታ ቁጥጥር ዉጭ የሆኑ እና የኢኮኖሚው መዋቅር አካል ያልሆኑ ሆኖም ግን የአባላትን ወይም የማኅበረሰብን የጋራ ችግር ለመቅረፍ ወይም የጋራ ደስታን ለመፍጠር የሚቋቋሙ ማኅበራትን ነው «ሲቪል ማኅበራት» ብለን የምንጠራቸዉ።

ሲቪል ማኅበራት (Civil society) ሰዎች በራሳቸዉ ፈቃድ፣ ሳይገደዱ ለጋራ ፍላጎቶቻቸዉ፣ ጥቅሞቻቸው እና እሴቶቻቸው መሟላት የሚከውኗቸውን የጋራ ተግባራት ለማስተባበር አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሚፈጥሯቸዉን አደረጃጀቶችን ሁሉ ይመለከታል። የእነዚህ ማኅበራት ጥንቅር ደግሞ ሲቪል ማህበረሰብን ይፈጥራል። ሲቪል ማኅበረሰብ ከቤተሰብ፣ ከመንግስት እና ከገበያ (በሌላ አነጋገር ከቤተሰብ፣ ከፓለቲካና ከኢኮኖሚው መዋቅሮች) የሚለይ ቢሆንም ከሁሉም ጋር ትስስር አለው። መንግሥታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶችን፣ የማኅበረሰብ ስብስቦችን (community groups) የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሙያ፣ የእምነት ማኅበራትን፣ ራስ-አገዝ ድርጅቶችን፣ የአድቮከሲ ቡድኖችን፣ የነፃ ሚዲያ አካላትንና ማኅበራዊ ንቅናቄዎችን በሲቪል ማኅበራት ምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

አንድ ማኅበር ነፃነቱ በመንግሥት ከተነጠቀ ሲቪልነቱ ይቀራል። በዚህም ምክንያት ወያኔ የሚያደራጃቸው የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የገበሬዎች፣ የሠራተኞች .... ወዘተ ማኅበራት በመነሻቸዉ ጀምሮ ሲቪል አለመሆናቸዉን ልብ ይሏል።

## ሲቪል ማኅበራትና ማኅበራዊ ካፒታል

ሲቪል ማኅበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ በተጨማሪ ለማኅበረሰቡ የሚያበረክቱት ትልቅ አስተዋፅዖ አለ - ማኅበራዊ ካፒታልን መፍጠር እና/ወይም ማጎልበት።

ማኅበራዊ ካፒታል /social capital/ የሰዎች አብሮ የመሥራት ችሎታ ነው ተብሎ በአጭሩ ሊተረጎም ይችላል። ትንሽ ዘርዘር እናድርገው ከተባለ ማኅበራዊ ካፒታል በማኅበረሰቡ አባላት መካከል ያለው መተማመንን፣ አባላት በተቋማት ላይ ያላቸው እምነትን፣ ማኅበራዊ ጉልበትን (social energy) ፤ ማኅበራዊ ክብር civic virtue ማኅበራዊ ስነልቦናን (community spirit) ፤ ማኅበራዊ ትስስሮችን (social bonds) ፤ ማኅበራዊ ህይወትን (community life) መልካም ጉርብትናን (good neighbourliness) ፤ ማኅበራዊ ከለላን (social ozone) አድማሱን ያሰፋ የጓደኝነት ስሜት (extended friendships) እና የመሳሰሉትን ሁሉ ይመለከታል። ማኅበራዊ ካፒታል የተለያዩ ቡድኖች ተዋደው፣ ተቻችለው፣ ተደጋግፈው እንዲኖሩ የሚያደርግ የአንድ ማኅበረሰብ ሙጫ ነው።

የአንድ ግለሰብ ትምህርት፣ ሙያ፣ ክህሎት፣ ዝናው የማይጨበጡ ሃበቱ (intangible assets) እንደሁኑ ሁሉ ማኅበራዊ ካፒታል የአንድ ማኅበረሰቡ የማይጨበጡ ሃብቶች ናቸው። ልክ ሙያ፣ ክህሎት፣ መልካም ስም የሌለው ሰው ድሃ እንደሆነ ሁሉ የዳበረ ማኅበራዊ ካፒታል የሌለው ማኅበረሰብም ድሃና የማደግ ተስፋውም የቀጨጨ ነው።

ወያኔ ሲቪል ማኅበራት ላይ የዘመተው የመረዳዳት፣ የመተጋገዝ፣ የመተዛዘን ባህላችን ጨርሶ ከአጠፋው በኋላ ያለብዙ ችግር እንደሚገዛን ስለሚያውቅ ነው። የባርያ አሳዳሪ ባሮች እንዲተጋገዙ፤ ወይም በጋራ ችግሮቻቸው ላይ እንዲወያዩ አይፈቅድም።

## ማኅበራዊ መተማመን

በሲቪል ማኅበራት አማካይነት የሚዳብረዉ የአባላት መተማመን ዋነኛዉ የማኅበራዊ ካፒታል ዓይነት ነዉ።

በርካታ ምሁራን (ለምሰሌ ሮበርት ፑትናም እና ፍራሲስ ፉኩያማ) የመተማመን እጦት የአንድን ማኅበረሰብ እድገት በእጅጉ እንደሚያቀጭጭ አበክረዉ ይናገራሉ። እንደ ፍኩያማ ከሆነ የአገሮች እድገት መጠን ከሚወስኑ ነገሮች ዋነኛው ማኅበራዊ መተማመን ነዉ። መተማመን ባለበት ማኅበረሰብ ውስጥ ችግር ቢደርስ እንኳን ተጋግዞ መፍትሄ ይፈለጋል። መተማመን በሌለበት ማኅበረሰብ ግን መተጋገዝ፣ መተባበር አይኖርም፤ ጉልበት የሚጠፋው በመነቃቀፍና በመወነጃጀል ይሆናል።

ወያኔ ሲቪል ማኅበራት ላይ የዘመተው ይህ እንደማኅበረሰብ የመዝለቃችን ዋስትና የሆነው ማኅበራዊ ካፒታላችንን ለማጥፋት እንደሆነ መገንዘብ ይገባናል። እናም ጉዳቱ የማኅበራቱ ተግባር መሰናከሉ ብቻ ሳይሆን በአባላቱ መካከል ሊዳብር ይችል የነበረዉ የመተማመን መጠን መጥፋቱም ጭምር ነው። ማኅበራዊ ካፒታልን ማውደም ግዑዝ ካፒታል (ለምሳሌ ድልድይን) ከማፍረስ እጅግ የባሰ ጉዳት ያስከትላል።

ወያኔ በተለያዩ መንገዶች ሲቪል ባህላችንን በመበከሉ በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ያለው የመተማመን መጠን ምን ያህል ዝቅተኛ እንደሆነ ሁሉም ሰው የሚያውቀው ጉዳይ ይመስለኛል። ገበያ ወጥታችሁ በርበሬ ከመግዛታችሁ በፊት ምን ያህሉ ቀይ አፈር ይሆን የሚለዉ ያስጨንቃችኋል - መቼም ንፁህ ነዉ ብሎ ማመን ቀርቷል። ንፁህን ማርን ከአምሮዓችሁ አውጡት ንቦቹ እራሳቸዉ ስኳር ስለለመዱ አበባ ፍለጋ መንከራተቱን ትተዉታል። የእርስ በርስ ጥርጣሬ እጅግ በመባዛቱ ሰው ሰላም ሲላችሁ እንኳን «ከምን አኳያ» ብላችሁ ጠይቁት ይባላል።

የእርስ በርስ ጥርጣሬ መብዛት ለወያኔ አገዛዝ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮለታል። አንድ ተጨባጭ ምሳሌ ልስጥ ተቃወሚ ፓርቲዎችን ለመበተን የስብሰባ ቃለጉባዔዎቻቸዉን በጋዜጣ ያትማል። «ማነው ምስጢር» የሚያወጣዉ የሚለው ጥያቄ የፓርቲዉን አባላት ሲያምስ ወያኔ ይስቃል። ከእንዲህ ዓይነት ጥርጣሬ ውስጥ ተኩኖ የረባ ነገር መፍጠር እንደማይቻል ግልጽ ነው።

በማኅበራዊ ካፒታላችን ክፉኛ መሸርሸር ምክንያት አብሮ መሥራት በሚያስፈልግበት ቦታ ሁሉ ኢትዮጵያዊያን ችግር ውስጥ እየገባን እንገኛለን። ባንድ ወቅት አንድ ሰዉ «በኳስ ጨዋታ ደካሞች የሆነው ያለ ምክንያት አይደልም፤ እግር ኳስ እስከ መጨረሻው ደቂቃ ድረስ መተጋገዝን ይፈልጋል፤ በሩጫ ግን በመጀሪያዎቹ ዙሮች ከተደጋገፍክ ትልቅ ነገር ነው፤ ወሳኝ በሆኑት የመጨረሻዎቹ ዙሮች ሩጫ የግል ነዉ፤ እኛ ይኸ ይመቸናል» አለ። ፓለቲካችን ይኸንን ሩጫ አይመስልም?

ኢትዮጵያ ውስጥ የሽርክና ንግዶች አማካይ እድሜ ሁለት ዓመት ተኩል ያህል እንደሆነ ይገመታል። መጀመሪያ ዓመት ላይ በፍቅር ያብዳሉ፤ ሁለተኛ ዓመት ላይ ይነጫነጫሉ፤ ሶስተኛ ዓመታቸዉን ሳያከብሩ ተፋልሰዉ ይለያያሉ። ይኸስ በፓርቲዎቻችንና በሲቪል ማኅበሮቻችን ላይ የሚታይ ባህሪይ አይደለምን?

የማኅበራዊ ካፒታል በተለይም ደግሞ የመተማመን እጥረት ድሮም ነበረብን፤ ወያኔ ደግሞ ይኸንን እጥረት አባባሰው። ባሁኑ ሰዓት ዜጎች በመንግሥት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በጓደኞቻቸውና በራሳቸዉም ጭምር እምነት እንዲያጡ የተደረጉበት ጊዜ ነው።

አንድ ሌላ ምሳሌ አንስቼ ወደ ሌላ ጉዳይ ልለፍ። ከቅንጅት መሪዎች መታሰርና መፈታት ጋር ተያይዞ የታዘብነው እጅግ አሳዛኝ ነገር ሽምግልና ላይ የደረሰው ውርደት ነው። ወያኔን ኅብረተሰቡ የሚያከብረውን «ሽምግልና»ን አዋረደ። ይህ ደግሞ ጉዳቱ ወደፊትም ሽማግሌዎችንም ሽምግልናንም እንድንጠራጠር ያደርገናል።

በሲቪል ማኅበራት ላይ ጫና ሲደረግ የምንጎዳው በጣም ስውር በሆነ ነገር ግን እጅግ በሚጎዳ ሁኔታ ነው።

**ይቀጥላል**

**ወያኔ በእነ ጄ/ል ተፈራ ማሞና በሌሎችም እስረኞች ..........(ከ ጽ 1 የዞረ)**

ብዙዎቹ እስረኞች በስኳር፣ በድምግፊትና በተዛማጅ በሽታዎች የሚሰቃዩ መሆናቸው ሲታወቅ፣ አሁን እየደረሰባቸው ያለው ድብደባና ሰቆቃ ህመማቸውን አባብሶ ለሞት ሊዳርጋቸው እንደሚችል ምንጮቻችን ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜናም የወያኔው ዘረኛና ርካሽ አገዛዝ በስታሊን፣ በመንግስቱና በኢዲአሚን ዘምን ይውሉ የነበሩ እስረኞችን የማሰቃያ መንገዶችን ሁሉ አሁን በእስር ላይ በሚገኙ አገር ወዳድ ዜጎች ላይ መፈጸሙ፣ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ማስቆጣቱን የሚደርሱን መረጃዎች ያሳያሉ።

ተስፋ እየቆረጠ የመጣው የማፊያው ና የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ይፈጸማል ተብሎ የማይታሰብ ድርጊት በእስረኞች ላይ መፈጸሙ በህዝቡ ላይ ያለውን ንቀት የሚያሳይ ነው የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን የዱርየ አገዛዝ በፍጥነት ለማስወገድ እንዲነሳም ጥሪ አቅርበዋል።

ዘረኛው ወያኔ እየተቀጣጠለ የመጣውን ህዝባዊ ተቃውሞ፣ ሰዎችን በመግደል፣ በማሰቃየትና በማሰር ሊወጣው እንደማይችል እየተረዳው በመጣበት በአሁኑ ጊዜ የአጥፍቼ ልጥፋ ፖሊሲውን በተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ላይ ተግባራዊ እያደረገ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። ቀደም ብሎ በኦሮሞ፣ በደቡብ፣ በጋምቤላና በኦጋዴን ተወላጆች ላይ ሲፈጽማቸው የነበሩትን አሰቃቂ ድርጊቶች አሁን ደግሞ በአማራ ተወላጆች ላይ እየፈጸመው መገኘቱም በርካቶች ይስማሙበታል።

የዜናውን ይፋ መሆንን ተከትሎ በተለያዩ ድህረገጾችም ላይ በርካታ አስተያየቶች እየተሰነዘሩ ነው። በኢትዮጵያን ሪቪው ላይ ከተጻፉት መካከል ኩምሳ የተባሉ ጸሀፊ " ድሮውንስ ከወያኔ ምን ይጠበቃል። የመለስ አገዛዝ ሰዎችን ዛፍ ላይ በመስቀል፣ ሴቶችን በመድፈር ፣ በማሰርና በማሰቃየት ነው የሚታወቀው። የናዚው መለስ አገዛዝ ሲንኮታኮት ብቻ ነው ነጻ የምንወጣው። ብለዋል።

መስታውት የተባሉ ጸሀፊ ደግሞ "ህዝቦችን ማሰቃየት ወያኔ የተካነበት ችሎታው ነው። አገሪቱ የምትገኘው በወያኔ የማጎሪያ ካምፕ ውስጥ ነው። ይህን ካማፕ ለማፍረስ ሁላችንም በአንድነትና በፍጥነት እንነሳ " ብለዋል።
በኢትዮጵያን ሚዲያ ፎረም ላይ ካራቺ የተባሉ ጸሀፊ ደግሞ " እውነት ይህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ይፈጸማል። እኔ ድርጊቱን ማመን ነው ያቃተኝ። በቃ እኔ እነዚህን ሰዎች ለመፋለም ወስኛለሁ። ሁሉንም ነገሬን ለትግል ለማዋል ቆርጫለሁ" ሲሉ ተናግረዋል።

ሌላው ደጀኔ የተባሉ አስተያየት ሰጪ ደግሞ " ወያኔ እንዲህ አይነቱን ዘግናኝ ድርጊት በምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች ላይ መፈጸሙ ያሳዝናል። እስረኞቹ የኢትዮጵያ ጀግኖች ናቸው። ስጋቸው እንደ ሽንኩርት ቢከተፍ፣ መንፈሰቻው ግን ከወያኔዎች በላይ ነው። አሸናፊዎች ናቸው። የወያኔ ድርጊት ከሰው ተራ አስወጥቶ አውሬ አድርጎታል። እናሸንፋለን። ጄ/ል ተፈራ ማሞ፣ ጄ/ል አሳምነው ጽጌና ሌሎችም እስረኞች ለዘላለም ይኑሩ፣ ታሪክም ጀግንነት ለተሞላው ስራችሁ ዘላለም ሲያስታውሳችሁ ይኖራል" ሲሉ አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

## በወያነ መንደር ትርምሱ ቀጥሏል. (ከገጽ 1 የዞረ)

አሰፋ ከሲቶበፖሊሶቹ ከፍተኛ ወከባና እንግልት በሚደርስባቸው ጊዜ ግራ ተጋብተው፡-" እኔኮ ከፍትሕ ሚኒስትርነቴ ብነሳም የፕሬዚዳንቱ ፅህፈት ቤት ተሿሚ ነኝ፤ ይህን ቤት ልቀቅ መባሌን ለፕሬዚዳንት ግርማ ነግሬያቸው፤ እርሳቸው ከጠቅላይ ሚኑስትሩ ጋር በመነጋገር የቀድሞ ጥቅማ ጥቅሜ እንዲከበር ስላስወሰኑልኝ -ውሳኔውን እስካመጣ ድረስ ታገሱኝ" ብለው ፖሊሶቹን ቢማፀኑም፤ ነገሩ ሁሉ የ አህያ ባል-ከጅብ አያስጥልም ሆኗል-ብሏል ዘጋቢያችን።

ምክንያቱም ከቤቶች ኤጀንሲ ቤቱን ለማስለቀቅ የመጣው ግብረ-ሀይል ቡድን አባላት- ምክንያታቸውን እንደማይቀበለውና የእነሱ ተግባር ከበላይ አካል አድርጉ የተባሉትን ማድረግ ብቻ እንደሆነ ይነግሯቸዋል።

ቀድሞ የሰጡት ምክንያት ውሀ እንዳልቋጠረላቸው የተረዱት የቀድሞው ፍትህ ሚኒስትርና የአሁኑ የፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ተሿሚ ተብየው ምክንያታቸውን በመቀየር፡-"ዕቃየን የማስቀምጥበት ፤ እንዲሁም ባለቤቴንና የስድስት ወር ህፃን ልጄን የማኖርበት ቦታ ስለሌለኝ እባካችሁ ታገሱኝ" ብለው ፖሊሶቹ እግር ስር ቢወድቁም፤ከፖሊሶቹ ያገኙት መልስ ይበልጥ የሚያስደነግጥና ኩሽ የሚያደርግ ነበር- " ትዕዛዙን ነግረነዎታል፤ የማይሰሙን ከሆነ ቤቱን አሽገን እርስዎን ፖሊስ ጣቢያ ለመውሰድ እንገደዳለን"የሚል።

በዚህን ጊዜ ተስፋ የቆረጡት አሰፋ ከሲቶ ፡-" ያው የምትፈልጉትን ሁሉ ማድረግ ትችላላችሁ" ማለታቸውን ተከትሎ፤ ቤት አስለቃቂው ግብረ-ሀይል -ቤቱን በማሸግ ከነሚስታቸውና ከህፃን ልጃቸው ጋር ሜዳ ላይ ጥሏቸዋል።
በጉዳዩ ላይ ያነጋገርናቸው አንዳንድ ወገኖች ፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቱባ ባለስልጣን የነበሩትና የምርጫ 97 ቀውስን ተከትሎ በተፈጠረው አገራዊ ችግር -ወያኔ ዋነኛ የተቃዋሚ መሪዎችን ለመምታት በህግ ሽፋን ከነ ፊታውራሪ ሽመልስ ከማል ተርታ በደጃዝማችነት አሰልፏቸው የነበሩት አሰፋ ከሲቶ እንዲህ የቀለሉት ፤የሽንኮራነት ጊዜያቸው በመጠናቀቁ እንደምጣጭ ስለተጣሉ ነው ሲሉ፤ ሌሎች ግን፡- " ምክንያቱ እሱ ብቻ አይደለም-ሰውየው የደቡብ ሰው በመሆናቸውም ጭምር ነው" ባይ ናቸው።

እኚህ ወገኖች ለዚህ አባባላቸው እንደማስረጃ የሚጠቅሱት " ኢህአዴግ" በሚል ሽፋን የተሰባሰበው ቡድን ፤የጥቂት የህወሀት ቱባ ሹመኞች የግል ፍላጎትና የተበላሸ ፖለቲካዊ አመለካከት ማስፈፀሚያ መሳሪያ እንጂ፤ ሚዛናዊ ሀልወት ያለው ያለመሆኑን ነው።

የመለስ አገዛዝ፤ራሱን " የብሔረሰቦች ነፃነት ተሚጋች ነኝ"በማለት ቀደም ካሉት ዓመታት ጀምሮ በድጋፍ ስም በየክልሎች የበላይ ጠባቂ ሞግዚት እያለ ቱባ የህወሀት ሰዎችን ሲሾምና ሲያነግስ መቆየቱን ያስታወሱት እነዚህ ወገኖች፤ነፃ ወጡ የተባሉት ክልሎች በራሳቸው አስተዳደር የበይ ተመልካች-ጥቂቶቹ የመለስ ሰዎች ደግሞ በሰው ክልል ፈትፋች ሆነው ለዓመታት ሲዘርፉ መኖራቸውን ያወሳሉ።

"እንደውም ይላሉ..." እኚሁ ወገኖች የክልል ጠባቂ ሞግዚት በሚል ስም የተሾሙት የህወሀት ሹመኞች እፈፀሙ ያለውን ግፍ መረጃ ዋቢ አድርገው በምሬት ሲጠቅሱ".....እንደውም በአንዳንድ ክልሎች የተሾሙት የመለስ ሰዎች የክልል ፕሬዚዳንት ተብየዎቹን በጥፊ እስከመማታት ደርሰዋል"
ሆኖም፤ራሳቸው ባሪያ ሆነው ለሌሎች ነፃነት ሊሰጡ ስለማይችሉ እየፈፀሙት ያለው ግፍ የሚደንቅ አይደለም ያሉት እኚሁ አስተያዬት ሰጪዎች፤ አሰፋ ከሲቶም የዚህ ዐይነት ድርጊት የተፈፀመባቸው በብሔረሰብ ተዋፅኦ ስም የይስሙላ ተሿሚ በመሆናቸው ለመሆኑ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል ብለዋል።

**ከ9 ሚልዮን በላይ ህዝባችን በከፍተና የርሃብ አደጋ .(ከገጽ 1 የዞረ)**

የኢትዮጵያ ህዝብ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በረሀብ፣ በመብራት እጦትና በበሽታ እየተሰቃየ እንደሚገኝ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ የመለስ አገዘዝ አገሪቱን ለማስተዳደር አቅም እያጠረውና ተስፋ እየቆረጠ መምጣቱን ምንጮች አክለው ገልጸዋል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ የሚገኘውን የመለስን የሸፍታ ቡድን ለማባረር እንቅስቃሴዎች የተጀመሩ ሲሆን፣ ግንቦት 7 የኢትዮጵያን ህዝብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከድህነት፣ ከአምባገነኖች መዳፍ፣ ከረሀብና ከተዛማጅ በሽታዎች ለማላቀቅ ከፍተኛ ትግል በማድረግ ላይ መሆኑ ይታወቃል። የአፈጀና የገረጀፈውን የመለስን የዘረኛ አስተዳደር ለማንኮታኮት፣ በምትኩም ዲሞክራሲያዊት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመመስረት ሁሉም ኢትዮጵያዊ መረባረብ እንዳለበት የተለያዩ ወገኖች በመናገር ላይ ናቸው።

አምባገነኑ መለስ ወደ ስልጣን ሲመጣ ህዝቡ የተሻለ በልቶ ማደር ይችል እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን፣ በደረቁ የወያኔ ዘመን ግን ህዝቡ በቀን አንድ ጊዜ እንኳን መብላት እየተቸገረ ጾሙን እንደሚያደር ከኢትዮጵያ የሚላኩ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከ9 ሚልዮን በላይ የሆነው ህዝባችን አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ካላገኘ በከፍተኛ አደጋ ለይ እንደሚወድቅ በትናትናው ዕለት ይፋ ያደረገው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የቀረበው የማስጠንቀቂያ ሪፖርት የጁቡቲ ወደብ ከአቅም በላይ በመጣበቡ ምክንያት የ'ዕርዳታ እህሉን ማስገቢያ ወደብ ችግር እንደተከሰተ ጭምር ገልጾአል::

የ'ኤርትራው ፕረዝደንት ኢሳያስ አፈወርቂ በቅርቡ ኢትዮጵያን ሮቪው ለተባለ ድህረገጽ አዘጋጅ በሰጡት ቃለመጠይቅ አስቸኳይ የ'እርዳታ ምግብ ለተረጂው ወገናችን በአሰብ ወደብ በኩል እንዲገባ ኤርትራ ያሳየቺውን በጎነት ለአገሩና ለህዝቡ ደንታ የሌለው ዘረኛው የመለስ ዜናዊ መንግስት እንዳልተቀበለው አጋልጠዋል::

በተለይ 80 ሚሊዮን ህዝብ የሚኖርባት አገር በአንድ ወደብ ብቻ ጥገኛ መሆኗና የጂቡቲ ወደብም በመጨናነቁ ከአለም በልመና የተገኘውን እርዳታ በጊዜ ለማስገባት አለመቻሉን ዜናው አክሎ አብራርቷል።

**የወያኔ ሁለገብ ዘረፋ መጋለጡን ቀጠለ (ከገጽ 1 የዞረ)**

የሃይማኖት ተቋማት የመጀሪያዎቹ የጥቃት ሰለባ ሆኑ፤ በማከታተልም የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት ተያዙ፤ ከዚያም የሙያ ማኅበራት ተጠለፉ፤ ቀጥሎ ግብረሰናይ ድርጅቶች በህግ ሰንሰለት ታሰሩ፤ እያለ .. እያለ .. ወረደና ባሁኑ ሰዓት የስፖርት ቡድኖች፣ ሰንበቴዎች፣ እድሮችና እቁቦች ሳይቀሩ በወያኔ ቁጥጥር ሥር የማድረግ ሥራ ተያይዞታል፡፡ በዚህ ከቀጠለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቡና ተርቲቦችም የወያኔ መፈንጫ ይሆናሉ፡፡


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org